# ማን ያውራ የነበረ 9

ሁሌም ሰማዕት የምትሻ ሀገር ያልታደለች ናት ተብሏል፡፡ የባሰች ያልታደለች ሀገር ግን እሪ ብላ ስትጮህ፤ጠላት ሊቀራርጣት ሲገዘግዛት ኡኡ ስትል ሰሚ የምታጣዋ ናት፡፡ ኢትዮጵያ የወያኔ ተምች ከወረራት ጊዜ ጀምሮ የኋለኛቷ የባሰባትን መስላለች፡፡ ሄርማን ኮኸን የተባለ የጠገበ አሜሪካዊ በብጣቂ ወረቀት ላይ በለንደን ከተማ ዕፎ የወያኔን ባልስልጣንነት በሕዝብ ላይ ሲጭን ሀቀኛ ልጆቿ ሲጮሁላት፤ ተማሪዎች በአዲስ አበባ ተሰልፈው ሲሞቱላት ብዙዎች ያስተማረቻቸውና የከበሩባት ግን ከድተዋት ለወራሪዋና ለገነጣጣይዋ ድጋፍ ሲሰጡ ታይተዋል፡፡ ወዲያውም ዘረኛው ቡድን በቀደደው ቦይ ለሽ ብለው ሊፈሱ የየብሄረሰባቸውን ቡድንና ተለጣፊ ድርጅት መስርተው፤በሽግግሩ ጉባዔ በፈረደበት ነፍጠኛ ላይ ከመለስ ዜናዊ ጋር አብረው ቧርቀው፤ ይሸንሽን ገላዋን በኢትዮጵያ ላይ ዘፍነው፤ ወያኔን ይታገሉ በነበሩት በኢሕአፓና በኢዴኃቅ ላይ አላግጠው፤ ሀገር አጥፊዎቹን ልጆቼ ብለው በሀገራችን ቁስል ላይ ጨው የነሰነሱትን ዛሬም የምንረሳቸው አይደለንም፡፡

ኢትዮጵያ ዛሬም የሚሞትላት ልጅ ፤የሚሰዋላት ጀግና ትፈልጋለች፡፡ ሀገር ናትና ዜጎች ተብዬዎቿ የት አሉ ማለቷም አያስደንቅም፡፡ ሲያልፍላትና ሲያምርባት ብቻ ውድ ሀገሬ የሚሏትን አትፈልግም፡፡ ለጫጫታው ከሆነማ ለሀገር ነፃነት ሲሉት ቅንጣትም እርዳታ የማያደርገው ሁሉ ኢትዮጵያዬ እያለ ይዘፍንላታል፡፡ ትላንት ልጆቿን የፈጀው ሁሉ ዛሬ የኢትዮጵያዊነት ምሳሌ እኔ ብቻ ነኝ ሊላት ይቃጣዋል፡፡ የቃል ክቡርነት ቃሉን ለሚያከብር ብቻ ነው መባሉ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ነው፡፡ መለስ ዜናዊ ምርጫ ብሎ በጀመረው የጠነዛ ቧልት ዙሪያ ድርጅት ተብለው የተመዘገቡና የሚወዳደሩ የሚለውን ዝርዝር ስናይም የዚህ መሰሪ ቡድን ከፋፍላቸው ተልዕኮ ምን ያህል እንደተሳካም እንገነዘባለን፡፡ ዘር ቆጥሮ ተደራጅሁ ያለው ቁጥሩ ቀላል አይደለም፡፡ የወያኔ ዕቅድ ውድቀቱ ግን ብዙዎቹ ኢትዮጵያዊነትን አንክድም ብለው መነሳታቸው ላይ ነው፡፡ መርዙ ግን ትላንትም ዛሬም ብዙዎችን አልበከለም ማለት ሀሰት ይሆናል፡፡

ኢሕአፓ ከተመሰረተበት ከ 33 ዓመት በፊት ጀምሮ ስሙም ዓላማውም፤ተግባሩም አቅዋሙም ኢትዮጵያዊ ሆኖ የቀጠለ በመሆኑ <u>ሀገር ሲል፤ሀገር ወዳድነት ሲል</u> ከብዙዎች መለየቱ አልቀረም፡፡ ሀገር ፍቅሩ የይስሙላ ስላልነበረም አክራሪ ተብሎ፤ ትምክተኛ አባ ኢትዮጵያ የአማራ ድርጅት ተብሎ በመጠቃት የከፈለው ዋጋ በቀላሉ አይገምትም፡፡ ኢሕአፓ ሀገር ሲል በባንዲራ ዙሪያ ባዶ ቡራ ከረዩን በማሰማት፤የሚች ፍሬው ኃይሉን መከታ ጋሻዬን በመዝፈን፤ ወይም ብዙሁት ሊገቡ በማይችሉበት ሆቴል መቶና ከዚያም በላይ መንገድ አዳሪ ህፃናትን ሊመግብ የሚችል ገንዘብን ባስወጣ መጠጥ ተሟሙቆ ኢትዮጵያ ሀገሬ ብሎ መጮህን ማለቱ አይደለም፡፡ ኢሕአፓ ኢትዮጵያ ሲል መጀመሩያ ሕዝቧ ማለቱ ነው፡፡ የሕዝቧ ቁጥር ደግሞ ከጥንቶቹ ከ500 አንበልጥም ባይና ከዛሬዎቹ ከአድዋ፤ ሽሬና አክሱም ማለትም ከአሽአ ምርጦች ሌላ ማን ተቆጥሮ ከሚለው ባሻገር ሰፊውን ሕዝብ የሚጠቀልል ነው፡፡ ስለዚህም የሀገር ትርጉም ሆነ በሀገር መኩራት፤ ለሀገር መሰዋት ሆነ ኢትዮጵያዊነት ለኢሕአፓ ያለው ትርጉም ከአስመሳዮቹ በጣም የተለየ ነው፡፡ ሀገርን ሲወዱ ሲያፈቅሩ ያው እንደልጅ ቢሆንም በሀገር ስም ወንጀል ሲሰራ መቃወም ደግሞ ሀገራዊ ግዴታ ነው፡፡ ሰሞኑን በአዲስ አበባ እየተካሄደ ያለው የራስ ተፈሪያኖች በዓል ለምሳሌ ወያኔ ለፖለቲካው ዓላማው ሊጠቀምበት

መነሳቱን ስንጠቁም የሚቹን ዘፋኝ ቦብ ማርሌን ሚና ለማሳነስ ሳይሆን ሀገር ሰላም ነው ወዘተ  ብሎ በበዓሉ ሊጠቀም የተነሳውን ወያኔን ለማጋለጥ ነው:: መለስ ዜናዊ ግሩም ድንቅ የሚለው ክስተት የእኛ አይጠቅሜ ወይም ፍዳ መሆኑን በማወቅም ነው:: ሀገር ተቀምተናልና የመነሻችን መጀመሪያ ሁሌም ይህ ጉዳይ ነው:: ከመለስ ዜናዊና ሚስቱ ጋር በአደባባይ ለመጨፈር ፍላጎቱም ሆነ የዝቅጠቱ በሽታ የለብንም:: በሼራተን ሆቴል ከእነ ስዩም መስፍንና ስብሀት ነጋ ጋር መሳከር፤ ወያኔን ተለማምጦ መነገድና ለመክበር መጣር፤ ቤት መስራት ወዘተ ለእኛ የትግላችን ግብ አይደለም:: መለስ ዜናዊ የሚጠላት ሀገር ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ፤ ሎሌው ዳዊት ዮሐንስ የፓርላማ አፈ ጉባዔ ወይም የወያኔ ቱሪናፋ ሆኖ ባለበት የፓርለማ ተመራጭ ነን በሚል ከድህው ሕዝብ ገንዘብ በደሞዝ መልክ ለመቀማትና ነጋ ጠባ ለመዋረድ ከቶም ፍላጎት የለንም::  ይህ ዓይነቱ የቅሌተ ፖለቲካ ሲያልፍም አይነካንም::

ሕዝብ ይቅደም ስንልም የሀገሪቷ ሕዝብ ሀሉ በዜጋነቱ እኩል ሆኖ የሚኖርባት ሀገርን ለመመስረት የምንችለው በዚህ መልክ ብቻ በመሆኑ ነው:: ለዚህም ነው ኢሕአፓ ትላንትም ዛሬም ትምክህተኛነትንና ጠባብ ብሄርተኛነትን ሲታገል የቆየውና እየታገለም ያለው:: ክልል አንደኛና ክልል ዜሮ እንዳይኖር ማለት ነው:: ሀገር ስንል ሕዝብ ማለታችን እስከሆነ ድረስ ሕዝብን እያጠፉ ሀገርን የሚገነባ ኃይል ሊኖር ይችላል ብሎ ኢሕአፓ አይቀበልም:: ስለዚህም  ፀረ ሕዝቡ የመንግስቱ  ኃይለማርያም አገዛዝ  በሀገር አጥፊነት ይፈርጃል እንጂ ትዝታዎቹ ወይም ነበረ  በሚል አረመኔን ስርዓት ሊያቆነጃጁ እየጣሩ ካሉት ጋር አይሰለፍም:: ማን ይውቀስ የደማ ነውና ያ ሁሉ የፈሰሰ የሕዘብ ደም ዛሬ ያንን ስርዓት ሊሞሽሩ የሚነሱትን ሁሉ ይወነጅላቸዋል:: የአፄ ኃይለስላሴ ምስል በአብዮት ወይም መስቀል አደባባይ ሲታይ፤ ኃይሌ ኃይሌ ብሎ ሲዘፈን ያ የአፄው ስርዓት የፈጀውን ና ያሰቃየውን ንፁህ ኢትዮጵያዊ መርሳት የማንችለው እኛ ዳግም ሕዝብ ሊገደል ነውና መቃወማችን የግድ ነው:: በመሰረቱ ለሕዝብ አንድነት ትግል ሲካሄድ የሀገሪቷን መከራ ከሚያበዙት ጎን የነበሩ፤ በሕዝብ ፍጅት የተሳተፉ፤ ሀገርን ከበዝባዥ ጋር አብረው የተቀራመቱና ሀገርን አጥፊን አገዛዝ ያገለገሉ ሁሉ ዛሬ ተመልሰው ከእኛም በላይ ኢትዮጵያዊ ለአሳር ብለው ሳያፍሩ ከመሰየም በተጨማሪ ለሀገር ሲታገልና ሲቃይ የባጀውን ኃይል ለመወንጀል ሲነሱ መታዘቡ መቸም የምፀት ምፀት ሆኖ ይገኛል::

ሀገር ወዳድ ከሆንን የመጣውን ስርዓት እናት ለልጇ የምትሰጠውን ልጅን ሲወዱ ክእነአ.ንትት ፍቅር መስጠት አይቻልም/አይጠበቅም::የአገዛዝ እንትት ሀገር ኡ/ፌ ነው ሁሌም:: ሀገርና መንግስት አንድ አይደሉም:: እንኳን በዕብሪት በስልጣን የተሰየሙ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ቀርቶ በሕዝብ ምርጫ እንኳን ለስልጣን የበቃ ኃይል ሀገርን ተክቶ ሊቆም አይችልም:: ሀገር ወዳድ ነን ስንል፤ በሀገራችን እንኮራለን ስንል በሀገር ስም አገዛዙ ወንጀል ሲፈፅም እሰየው እንላለን፤ ገበና ብለን ደብቀን እናጨብጫባለን ማለት አይደለም:: ኢሕአፓ ቀደም ሲል በደርግና ዚያድ ባሬ ጦርነት ጊዜ የወሰደውን አቅዋም በተመለከተ አረመኔው የመንግስቱ ኃይለ ማርያም ቡድንና ጭፍሮቹ ያኔም ዛሬም ድርጅቱ ዚያድ ባሬን/ሶማሌን ደገፈ ብለው ቢቀላምዱም የኢሕአፓ አቅዋም ግን የሶማሊያን ወረራ ተቃውሞ ደርግም ይህንን በመጠቀም ተቃዋሚን ሊያጠፋ መነሳቱን ጠቁሞ የኦጋዴን ሕዝብም መበደሉን መርሳት አይገባም የሚል ነበር:: ዚያድ ባሬም መንግስቱም በሕዝብ ትግል ካልተወገዱ ሕዝብን ያፋጃሉ ነበር ያለው:: በወያኔና ሻዕቢያ ጦርነትም

ወቅት ኢሕአፓ የወያኔ ድንገተኛና የይስሙላ ኢትዮጵያዊነት ሊዋጥለት ስላልቻለ ሕዝብ በመለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሳይወናበድ በቀውሱ ተጠቅሞ ሀገርን እንዲያስከበር ጠቁሞ ነበር፡፡ ከመለስ ጎን ቆሞ፤ገንዘብ ለግሶ፤ የመለስን ወያኔያዊ እርምጃ ሁሉ ደግፎ እሪ አላለም፡፡ በመለስ ትዕዛዝ ስር ያለ ጦርም አሰብን ያስመልስልናል ብለው ለቢረቁት የሰጣቸው መልስ አይ ሞኞች ስንቴ ትታለሉ የሚል ነበር፡፡ በመለስ ትዕዛዝም ኤርትራኖች አለአግባብ ሲባረሩ በቅድሚያ መለስ ወደ እናት ሀገሩ ይመለስ አለ እንጂ ኢሕአፓ ይህን ሀገር አስገማች ህገ ወጥ እርምጃ አልደገፈም፡፡ ከባድሜ መልስ ወደ መለስ ብለው ሊያዘናጉ የሞከሩትንም አጋልጧል፡፡ ቀንበርን ከተሸከሙ በኋላ መፈራገጥ እንደማይጠቅም አሳስቧል፡፡ ዛሬ ግልፅ እንደሆነውና ትላንት አብረውት ሕዝባችንን ሲያሰቃዩ የነበሩና ዛሬ የለም ተቃዋሚ ነን እያሉ ያሉ ግለሰቦች እንደመሰከሩት መለስ ዜናዊ አቀዋሙ መቸም ቢህን ኢትዮጵያዊ አልነበረም፡፡ በሀገር ፍቅር ሽፋን አድርባዮች ከገዢው ቡድን ጋር ሊሞዳመዱ ሲነሱ፤ በቀስ በቀስ ለዉጥ ሽፋን የደላቸው ለወያኔ ጊዜን ሰጥተው በሀገር ቅርጫው ሊካፈሉ ሲጥሩ ኢሕአፓ አደናቃፊ ጋሬጣ መስሎ ቢታያቸው አልተሳሳቱም፡፡ ነጋ ጠባ ቢዘምቱበትም አይደንቅም፡፡

ለኢሕአፓ ሀገር ማለት በቅድሚያ ሕዝብ ነው፡፡ ምርጦች ወይም የገዢው ቡድን ጭፍሮች ማለት አይደለም፡፡ በሀገሩ ሲኮራ በሕዝበ ነው የሚኮራው፡፡ በመለስ ዜናዊ አይኮራም፡፡ ፀረ ሕዝቦች ቢደነቁ ቢሸለሙ በውልደት ኢትዮጵያዊ ናቸውና ብሎ አይኩራራም፡፡ ሰፊው ሕዝብ፤አርሶ አደሩ፤ላባደሩ፤ መንገድ አዳሪው፤ደሀው ሕዝብ ምን ይላል፤ ምን ተጠቅሟል ነው ዋናው ጥያቄው፡፡ የወያኔ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ አይደለችም፡፡ ስለዚህ በጅምላና በደፈናው አንኮራባትም፡፡ በቅድሚያ ሀገራችንን ከቀማኛ ማስመለስ አለብን ማለት ነው፡፡ የሀገራችን ባለቤትና ባለመብት ዜጋ መሆን አለብን፡፡ የአክሱም ኃውልት ተመለስ ብሎ ለመፈንደቅ የሀገራችንን ቅርስ እየቸበቸበ ካለ አገዛዝ ጋር መስመር -መግጠም የለብንም፡፡ መለስ ዜናዊ ትላንት ጠግቦ ሳለ የአክሱም ሐውልት አይመለከታችሁም ያለንን ልንረሳም አይገባም፡፡ዋናውን ጉዳይ ከረሳን ማለትም ውሉን ከሳትን ሁሉም ይፈታብናልና ነው፡፡ ሕዝብ ደግሞ ትላንትን ከረሳ መከራውን ዳግም መሸከሙ አይቀሬ ነው፡፡መለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ ደርብ ብለው ሲጨፍሩ ልንቀላቀል ቀርቶ በቦታውም መገኘት የለብንም ማለት ነው፡፡

ዛሬ ሀገር ወዳድ ነን ብለው ግን ስራቸው ለወያኔ ዕድሜ ቀጣይ ሆኖ ያሉትን በተመለከተ ሕዝብ ነቅቶ ማወቅ አለበት፡፡ እንክርዳዱና ስንዴውን መለየት የግድ ነው፡፡ ሁሉም ፀረ ሕዝብ አገዛዝ ህሊናቸውን በሆዳቸው የለወጡ ሎሌዎችና ቅጥረኞች አሉት፡፡ በአምባገነኑ ዙሪያ ተኮልኩለው ፍርፋሪ እየለቀሙና አንዳንዴም የተቃዋሚ ጭምብል እያጠለቁ ሕዝብን ለማወናበደና ከፋፍለው ለገዢው ቡድን ሰለባ ለማቅረብ የሚራወጡ ነበሩ፤ ዛሬም አሉ፡፡ ሀገር ወዳድ ነን ቢሉም የሚያስቀድሙት የራሳቸውን አይታክቴ ከርስ ነው ወይስ የሀገርን ጥቅም ብሎ መጠየቅ ያሻል፡፡ ኢትዮጵያ ሀገሬ ያለ ሁሉ በእውን የዚች መከረኛ ሀገር ሀቀኛ ልጅ አይደለም፡፡ ይሞትላታል? ይሰቃይላታል? ማለትም ለሰፊው ሕዝብ ይታገላል ወይስ ከመለስ ዜናዊ ቡድን ጋር ይሞዳሞዳል? ለሹመት ለወንበር ይዋደቃል?
ማነው ሀገር ወዳድ?ማነው የኢትዮጵያ ሀቀኛ ልጅ? ወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑ ግልፅ ነውና ከመለስ ዜናዊ ሰምሮና ተባብሮ ያለ ሁሉ በሀገር ወዳድነት ሊፈረጅ አይችልም፡፡ ለከርስ አደር ሀገሩ ሆዱ ነው፡፡ ይህን መቸም መዘንጋት የለብንም፡፡

ኢሕአፓ በበኩሉ ግን የትግል ታሪኩን፤የሰማዕቱን ተጋድሎ፤ የዛሬም ፍፁም ኢትዮጵያዊ ይዘቱንና አቅዋሙን ዋቢ በማድረግ ድርጅቴ ኢሕአፓ ሀገሬ ኢትዮጵያ ብሎ አፉን ሞልቶ መናገር ይችላል።ለማንም ባዕድ ኃይል ተንበርክኮ ሀገርን አልሸጠም አልከዳምና የሚያፍርበት ታሪክ የለውም። ሀገር ሲል ሕዝብ ነውና የጠባቦችና የትምክተኞች ነቀርሳም አልነካውም። ወደፊትም የሚነካው አይሆንም። ለሕዝብ የሚታገል፤ለኢትዮጵያ የቆመና የሚዋደቅም ነውና ባዕድም ሆነ የመለስ አገዛዝ ለሚያወዛውዙት እንቁልልጭ ና ፍርፋሪ ውሰድ አይጥረበረብም። ታሪክና ሕዝብ ምስክሩ ናቸው። ለዚህም ነው ከሀዲዎች እየዘሙተበት በዘመቻቸው ሀቀኛ ኢትዮጵያዊነቱን ሳይወዱ የሚመሰክሩለት።